Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 228002

Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment ቀን መጋቢት 28 2015ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት - አቃቤህግ አለምፀሐይ ጉታ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ሰብለ ከበደ- ወኪል በረከት በርሄ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ189896 በ30/10/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 280819 በ5/7/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ26/9/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በስር የፌ/መ/ደ/ፍቤት በአመልካች(ስር 1ኛ ተከሳሽ) እና አሁን የሰበር ክርክሩ ላይ በሌሉት ወ/ሮ ተካበች ካሳሁን(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ላይ ባቀረቡት የተሻሻለ ክስ የተጠሪ ወላጅ አባት ኮሎኔል ከበደ ገድሌ በ9/2/76ዓ.ም እንዲሁም ወላጅ እናቴ በ1/6/02ዓ.ም የሞቱ ሲሆን ተጠሪ የወላጆቼን ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ፡፡ የተጠሪ ወላጆች በህይወት በነበሩበት ወቅት ክስ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የቀረበበትን የቤ.ቁ 761ን ጨምሮ የቤ.ቁ 760፤ 762 የሆኑ ባለ 4 ደጃፍ ቤቶችን ሰርተው ባለቤት ሆነዋል፡፡ የቤቶቹ ይዘት 139ካ.ሜ ሲሆን ቤቶቹ በተጠሪ ወላጆች ስለመሰራታቸው በቀድሞ አጠራሩ የከፍተኛ 14 ቀበሌ 14 ጽ/ቤት በ14/11/76ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ እንዲሁም የቤቶቹ የባለቤትነት ደብተር በ14/2/83ዓ.ም በተጠሪ እና በተጠሪ እናት ስም የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በጻፈው የባለቤትነት ደብዳቤ አረጋግጦልናል፡፡ ቤቶቹ የተጠሪ ወላጆች ሀብት መሆናቸው ተረጋግጦ መጀመሪያ ከወላጅ አባቴ በኋላ በውርስ ወደ ተጠሪ እና ወላጅ እናቴ ስመ ሀብቱ ተዛውሮልን በማይንቀሳቀስ ንብረት ማዛወሪያ ተመዝግቦ የቤትና ይዞታ ይዞታ ማረጋጋጫ ሰርተፍኬት በ25/1/77ዓ.ም ተሰጥቶናል፡፡ ከዚህ ግዜ ጀምሮ በቤቶቹ እና በይዞታዎቹ ላይ ግብር ስንከፍል ቆይተናል፡፡ ለቤቶቹም የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ለተጠሪ እና ለተጠሪ እናት በ14/2/83ዓ.ም ተሰጥቶናል፡፡ የቤቶቹ ስመሀብት ወደ ተጠሪ እና የተጠሪ አውራሽ ተዛውሮ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከአራዳ ክ/ከተማ ጽ/ቤት በ14/10/10ዓ.ም ተሰጥቶናል፡፡ የቤቶቹ ግብር እስካሁን በስማችን እየተገበረ ነው፡፡ ሆኖም ካርታው የቤ.ቁ 760፤ 761፤762 የሆኑ ባለ4 ደረጃ ቤቶች ቢሆንም የተጠሪ እናት ከሞቱ በኋላ ተጠሪ የማስተዳድረው የቤ.ቁ 760 እና 762ን ነው፡፡

የቤ/ቁ 761 የሆነውን ቤት አመልካች ያለህጋዊ ምክንያት ይዞ ለስር 2ኛ ተከሳሽ አከራይቶት እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ በተጨማሪም አመልካች በ2010ዓ.ም በደብዳቤ ካርታው የቀበሌ ይዞታ ያካተተ ስለሆነ ይምከን ብሎ ለአራዳ ክ/ከተማ ጽ/ቤት በመጻፍ አሳውቆኛል፡፡ ስለሆነም ለክርክር መነሻ የሆነው የቤ.ቁ 761 የሆነው ቤት ባለሀብትነት የተጠሪ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠኝ በመሆኑ አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል አቋርጦ የቤ.ቁ 761 የሆነውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክብ፤ ስር 2ኛ ተከሳሽም ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ባቀረበው መልስ ወ/ሮ ስነወርቅ አለማየሁ የተባሉ ግለሰብ በቤት ቁጥር 761 ከ1965ዓ.ም ጀምሮ ነዋሪ የነበሩ ሲሆን ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በኋላ እስከሞቱበት 27/12/03ዓ.ም ድረስ የቤት ኪራይ እየከፈሉ አልፈዋል፡፡ ባለቤታቸው እና ብቸኛ ወራሻቸው የነበሩ አቶ ገነነ አለሙ ከሞቱ በኋላ የሚቹ 2ኛ ሚስት ወራሽነታቸውን በማሳወጅ ለክርክር መነሻ በሆነው ቤት ላይ የስም ዝውውር አድርገውና ከአመልካች ጋር የአከራይ ተከራይ ውል ፈጽመው እየተገለገሉበት ለ48 አመታት ሲያስተዳድረው የቆየ በመሆኑ አመልካች የቤ.ቁ 761 የሆነው ቤት ባለቤት ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ የባለቤትነት መብት የላቸውም፡፡ አመልካች ይህን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ወርሶ እስካሁን እያስተዳደረው የሚገኝ ሲሆን በቅጽ 008 አማካኝነት ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ካዳስተር ኮድ ቁጥሩ የተገለጸ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ለቤቱም በአመልካች ስም በካርታ ቁጥር 053623 ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ሆኖም ተጠሪም በቤቱ ላይ ከዚህ ቀደም በ1977ዓ.ም በቁጥር 22810 ካርታ የነበራቸው ሲሆን ተጠሪ የያዙት የግል ካርታ በስህተት የአመልካች ንብረት የሆነውን የቤ.ቁ 761ንም አካቶ በመስራቱ ካርታው እንዲከለስና ማስተካከያ እንዲሰጥበት የአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 214/13 ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አራዳ ቅ/ጽ/ቤት በ14/3/13ዓ.ም አሳውቋል፡፡ ጽ/ቤቱም በ1977ዓ.ም በቁጥር 22810 የወጣውን የተጠሪን ካርታ ማምከኑን ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አራዳ ቅ/ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 378/13 በ29/3/13ዓ.ም አሳውቋል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቱም በ1977ዓ.ም በቁጥር 22810

በተሰጠው የተሳሳተ ካርታ አማካኝነት ለተጠሪ በይዞታ ልዩ መለያ ኮድ ቁጥሩ የተገለጸ ከካርታ ሌላ የተሰጠውን የካርታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተመሳሳይ ሁኔታ ማገዱን ለተጠሪ በደብዳቤ ቁጥር 46/02 በ30/3/13ዓ.ም አሳውቋል፡፡

በተጨማሪም በመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አራዳ ቅ/ጽ/ቤትም ተመዝግቦ ያለው የቤ.ቁ 761ን በተጠሪ ስም አሳስቶ የተሰራው የቀድሞ የካርታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አራዳ ቅ/ጽ/ቤት ሲስተም ተሰርዞ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የአራዳ ቅ/ጽ/ቤት የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በየስልጣናቸው ካርታውን ከማምከን ጀምሮ የመከነውን ካርታ የምስክር ወረቀት በማገድና ከሲስተም ውስጥ እንዲሰረዝ ውሳኔ ባስተላለፈበት ሁኔታ ተጠሪ የመከነና የታገደ ህገወጥ ካርታ፣ የካርታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይዘው መቅረባቸው ህጋዊነት ስለሌለው በቤ.ቁ 761 ላይ ያቀረቡት የባለቤትነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጠሪ የቤቱ ባለቤትነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ አመልካች ይህን ቤት ለረጅም ግዜ ኪራይ እያስከፈለ ከማስተዳደር ጀምሮ በቤቱ ላይ ህጋዊ ካርታና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች በተሟላ ሁኔታ በማደራጀቱ የቤቱ ህጋዊ ባለቤት በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ያላቀረቡና ክሱ ለመሰማት በተያዘው ቀጠሮም ስላልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት ታይቷል፡፡ ፍ/ቤቱም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ክሱን ከሰማ በኋላ ጭብጥ በመያዝ እንዲሁም የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ቁጥሩ በተገለጸ በ29/3/13ዓ.ም ለተጠሪ በ1977ዓ.ም በቁጥር 22810 የተሰጣቸውን ካርታ ያመከኑበትን ምክንያት ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የቤ.ቁ 761 የሆነውን ማህደር ከጽ/ቤቱ በማስቀረብ ከግራቀኙ ማስረጃዎች ጋር ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ላይ በ25/1/77ዓ.ም የባለቤትነት ማረጋገጫ ተሰጥቶ የነበረና ካርታውም ከላይ በተገለጸው መልኩ መምከኑ እና ለተጠሪ በዚህ ቤት ላይ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫም መታገዱ እንዲሁም ከሲስተም ላይ መሰረዙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው ካርታው ሊሰረዝ የቻለው የመንግስት ቤት በመሆኑ ነው በሚል ነው፡፡ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ፍ/ቤቱ ለሰጠው ትእዛዝ በሰጠው ማብራሪያ 6/7/13ዓ.ም በሰጠው ምላሽ በካርታ ቁጥር 22801 በ1977ዓ.ም በተጠሪ እና በተጠሪ ወላጅ እናት ስም የተሰጠው ካርታ አላግባብ የያዙትን የቀበሌ የመንግስት ቤት የሆነውን የቤ.ቁ 761 የሆነው ቤት ተካቶ ካርታው የተሰጣቸው በመሆኑ በ2010ዓ.ም በ1977ዓ.ም የተፈጠረውን መብት ብቻ መሰረት በማድረግ የመስክ ልኬት ሳይሰራ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መሰጠቱ አግባብ ባለመሆኑ እንዲሁም በ1977ዓ.ም የተፈጠረው መብት ላይ በካርታ ቢካተትም በአካል ያልያዙና በተቋሙ የመረጃ ስርአት ቅጽ 008 ላይ የቤ.ቁ 761 በቀበሌ የመንግስት ቤትነት ተመዝግቦ የሚገኝና በቤቱ ቁጥሩ 22801 የሆነ የተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመከነ መሆኑን ገልጿል፡፡

አመልካች ቤቱን አገኘን የሚለው በአዋጅ ቁጥር 47/67 ወርሰን ነው በሚል ሲሆን ቤቱ የተሰራው በተጠሪ አውራሾች መሆኑ አልተካደም፡፡ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ትርፍ ቤት በሚወርስበት ግዜ የወረሰውን ቤት፣ ግለሰብ ያስቀረውን የምርጫ ቤት የሚያሳዩ ቅጽ 003 እና ቅጽ 004 ተሞልተው የሚቀመጡ ሲሆን አመልካች ይህን ቤት ወርሻለሁ፣ ካርታውን ያመከነው አካልም

ካርታውን ያመከንኩት ቤቱ የመንግስት ስለሆን ነው የሚሉት ቤቱ ለረጅም ግዜ በመንግስት እጅ የነበረ እና በተቋሙ የመረጃ ስርአት ቅጽ 008 በመንግስት ቤትነት ተመዝግቦ ይገኛል በሚል ነው። ቤቱን የመንግስት መሆኑን እና በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት መንግስት የወረሰው ቤት መሆኑን የሚያሳይ ቅጽ 003 እና ቅጽ 004 በአመልካችም ሆነ ካርታውን ባመከነው አካል ባልቀረቡበት ሁኔታ በተቋሙ የመረጃ ስርአት ቅጽ 008 ቤቱ በመንግስት ቤትነት ተመዝግቦ መገኘቱ እና ለረጅም ግዜ በመንግስት እጅ መቆየቱ ብቻውን ቤቱን የመንግስት ቤት ሊያደርገው የማይችል ሲሆን ለአመልካች ካርታ የተሰጠው የተጠሪ አውራሽ ካርታ እንዲመክንላቸው ከጠየቁ በኋላ ካርታው ሊመክን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ከመወሰኑ በፊት ሲሆን ካርታውን ያመከነውም ሆነ ለአመልካች ካርታውን የሰጠው አንድ አካል በመሆኑ የተጠሪ አውራሽ ካርታ ሊመክን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ከመወሰኑ በፊት ራሱ ካርታ አዘጋጅቶ ሰጥቶ ለካርታው መምከን አንድን ምክንያት በአመልካች ስም ካርታ ተዘጋጅቶ መሰጠቱ ነው በሚል ያቀረበው ምክንያት ተቀባይነት የለውም።

ስለሆነም አንድን ቤት ለረጅም ግዜ መያዝ ብቻውን የባለቤትነት መብት የማያጎናጽፍ በመሆኑ እንዲሁም ቤቱ የቀበሌ/የመንግስት/ ቤት መሆኑን የሚያሳይ ቅጽ 003 እና ቅጽ 004 በሌሉበት ሁኔታ በተቋሙ የመረጃ ስርአት ቅጽ 008 በቀበሌ ቤትነት መመዝገቡ ብቻ ቤቱ በመንግስት የተወረሰ የቀበሌ/የመንግስት ቤት ነው ሊያስብለው የማይችል በመሆኑና ካርታውን ያመከነው አካል ካርታ እንዲመክን ጥያቄ ቀርቦለት ጉዳዩ በሂደት ላይ እያለ ካርታ ለአመልካች ሰርቶ በመስጠት የተጠሪን ካርታ በማምከን ለአመልካች ካርታ መስጠቱ አግባብ ባለመሆኑ፣ የተጠሪ አውራሾች ለክሱ መነሻ የሆነው የቤ.ቁ 761 የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተፈቀደላው መሆኑን ተጠሪ ባቀረቡት ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ ተጠሪ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1206 መሰረት በውርስ የተላለፈላቸውን እና አላግባብ የተያዘባቸውን ቤት ላአግባብ ከያዘው አካል ለማስመለስ የመፋለም መብት ያላቸው በመሆኑ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤ.ቁ 761 የሆነውን ቤት በተመለከተ በአመልካች እና ስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ሰው መካከል ያለው የኪራይ ውል ፈርሶ ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል።

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለረጅም ግዜ በመንግስት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ላአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ጥያቄውን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት እንዳለበት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 14095 ላይ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 እና አዋጅ ቁጥር 47/67 ጋር አያይዞ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። ይህም አንድን ቤት ለረጅም ግዜ በመንግስት እጅ መኖሩ ብቻ የመንግስት ነው ለማለት እንደማይቻል የሚያስገንዝብ ነው። በሌላ በኩል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 43600(ቅጽ 10) በፍ/ብ/ህ/ቁ 1677፣1845፣1206፣1188፣11192 መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደማይችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። ከዚህ አንጻር በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለረጅም አመታት ቤቱ በእጄ ነው በማለት የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ተቀባይነት የለውም።

ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሌላ በኩል አመልካች ካርታው መክኗል በማለት ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ የክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከሌሎች ቤቶች ጋር የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ቁጥሩ በተገለጸ በ14/2/83ዓ.ም የቤ.ቁ 760፣761 እና 762 የሆኑት ቤቶች ለተጠሪ አውራሽ የተሰጠ ስለመሆኑ የተሰጣቸው የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ ያስረዳል። ይህን ደብተር አመልካች ሰርዣለሁ፣ መክኗል ያለውን በተመለከተ የሚያመክነው ካርታውን የሰጠው አካል እንጂ የከተማ አስተዳደሩ ያልሰጠውን ማስረጃ መሰረዝ አይችልም። ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተጠሪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ ነው በማለት ውሳኔውን በማጽናት ወስኗል።

አመልካች ከላይ በተገለጹት ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች የመከና ካርታና ደብተርን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ተጠሪ ቤቱን አስተዳድረው በማያውቁበት ሁኔታ ለተጠሪ የባለቤትነትን መብት መፍጠሩ፣ ለአመልካች የተሰጠና የተረጋገጠ የተመዘገበ ካርታ ታሳቢ ባለማድረግ እንዲሁም አመልካች ቤቱን ለ48 አመታት በእጁ ይዞ እያስተዳደረ መገኘቱን ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ነጥቦች በመዘርዘር ውሳኔዎቹ እንዲሻሩ፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለው እንዲወሰንለት ጠይቋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የክርክር መነሻ የሆነው የቤት ቁጥር 761 በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ ለረጅም ግዜ በመንግስት እጅ የነበረ ከመሆኑም በላይ ቤቱን በሚመለከት ለተጠሪ በስህተት አላግባብ ተሰጥቷል የተባለው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመከነና በአመልካች ባለቤትነት የሚታወቅ ስለመሆኑ በተገለጸበት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት መንግስት የወረሰው መሆኑን የሚያሳይ ቅጽ 003 እና ቅጽ 004 በሌለበት ቤቱን የመንግስት ንብረት አያሰኘውም በሚል የተወሰነበት አግባብነት ከፍ/ብ//ህ/ቁ 1195፣1196፣ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33(2) አንጻር ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ4/11/13ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ28/11/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር እንዲጸና ጠይቀዋል።

አመልካች በ17/12/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል።

ማስረጃዎችን የመስማት፣ የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን የተሰጠው የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራቀኙ የቀረቡትን እና በትእዛዝ ያስቀረባቸውን ማስረጃዎች በመመርመር እና በመመዘን የተጠሪ አውራሾች ኮሎኔል ከበደ ገድሉ እና ወ/ሮ አስካለ ከበደ ለክሱ መነሻ የሆነው በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤ.ቁ 761 የሆነው ቤት የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን የመንግስት ለማድረግ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ ተጠሪ በተሻለ ሁኔታ ማስረዳታቸውን በፍሬነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው። ይህን ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤ.ቁ 761 የሆነውን ቤት ከሌሎች ይኀውም የቤ.ቁ 760፣761 እና 762 የሆኑት ቤቶች ለተጠሪ አውራሽ በወቅቱ ከነበረው ከከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ቁጥሩ 14/29/64 በሆነ በ14/2/83ዓ.ም የተሰጠ የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸው መሆኑንም ይግባኝ

Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment

ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያረጋገጠው ፍሬጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤ.ቁ 761 የሆነውን ቤት በተመለከተ በአመልካች እና ስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ሰው መካከል ያለው የኪራይ ውል ፈርሶ ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት የተሰሙትን ማስረጃዎች መርምሮ እና መዝኖ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 10(1) ከደነገጉት አንጻር ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ 189896 በ30/10/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 280819 በ5/7/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች እና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. በዚህ መዝገብ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 121685 እና 199896 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በ26/11/14ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ትእዛዝ የቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍቤት አራዳ ምድብ የኮ.መ.ቁ 189896 የሆነው መዝገብ በመጣበት አኳኋን ለፍ/ቤቱ ይመለስ፡፡
6. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/በ

Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment
Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment

ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም